# ኢትዮጰያ የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች ለማሳት በመልካም የለውጥ ምእራፍ ላይ ካሉ 20 ቀዳሚ የአለም አገራት አንዷ ሆነች: ጥናቶች

ኢትዮጵያ የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች በአጠቃላይ መመዘኛ ለማሳካት በመልካም የለውጥ ምእራፍ ላይ ካሉ 20 ቀዳሚ የአለም አገራት ተርታ እንደምትገኝ ሁለት አለም አቀፍ የዘርፉ ልማት ምርምር ተቋማት ትናንት ይፋ አደረጉ።

በተለይም ኢንድ ፖቨሪቲ የተባለ ድህረ ገጽ ትናንት ሁለቱ አለም አቀፍ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ምርምር ተቋማት ይፋ ያደረጉት የሚሊንየም ልማት ግቦች ስኬት ጥናት መሰረት በማድረግ ባወጣው ዘገባ የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች ለመሳካት በሁሉም መስክ እድገት እያስመዘገቡ ካሉ 20 አገራት መካከል ኢትዮጵያ በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት አገራት መካከል ትገኛለች።

ይህንኑ ጥናት ውጤት ይፋ ያደረጉት ኦቨር ሲስ ዴቬሎፕመንት ኢንስቲቲዩትና የተባበሩት መንግስታት ሚሊኒየም ግብ ካምፔይን የተባሉ የዘርፉ ምርምር ተቋማት ሲሆኑ ጥናቱ ይፋ የሆነበት አጋጣሚ ደግሞ ካናዳ ውስጥ የቡድን ስምንትና 20 የበለፀጉ አገራት ስብሰባ ለማድረግ እየተዘጋጁ ባሉበት ወቅት መሆኑን ድረ ገፁ ዘግቧል።

የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች በአጠቃላይ መመዘኛ ለማሳካት በመልካም የለውጥ ምእራፍ ላይ ካሉ 20 የአለም ሀገራት መካከል ቤኒን፣ ማሊ፣ ኢትዮጰያ፣ ጋምቢያ፣ ማላዊ፣ ቬትናም፣ ዩጋንዳ፣ ኔፓል፣ ህንድ፣ ካምፖድያ በቅደም ተከተል እንደሚገኙበትም ተቋማቱ በስእላዊ መግለጫ አስደግፌው ያወጡት ሪፖርት ጠቅሶ ድረ ገፁ ዘግቧል።

ሪፖርቱ እንደገለጹት ታዳጊ አገራት የልማት ግቡን ለማሳካት የሚያስችሉ ሁለገብ እድገት እያስመዘገቡ ነው።

እኤአ 2015 ድህነት፣ ማይምነትንና በሽታዎችን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ የአለም መሪዎች ያስቀመጡትን ግብ ለመምታት በርካታዎቹ ታዳጊ አገሮች ከፍተኛ እድገት በማስመዝገብ ላይ መሆናቸው ተመልክቷል።

በተለይ ነጻ የንግድ እንቅስቃሴንና ለዚህም ምቹና ወቅታዊ የሆኑ ሁኔታዎችን አገራቱ ማመቻቸታቸው ላስመዘገቡት እድገት ተጠቃሽ መሆኑንም የጥናት ተቋማቱ በመጥቀስ ድረ ገፁ አስታውቋል።

የምእተ አመቱን የልማት ግብ ለማሳካት እድገት ካስመዘገቡ 20 ታዳጊ አገራት መካከል 11ዱ በአፍሪካ እንደሚገኙ ጠቁሟል ።

ከነዚህ መካከል ኢትዮጵያ፣ ሞሪታንያ ፣ ጋምቢያ፣ ጋና፣ ማላዊ ቡርኪና ፋሶ፣ ዩጋንዳ፣ ሩዋንዳ፣ ኔፓል፣ ቶጎ እንደሚገኙበት አስታውቋል።

ግማሽ ያህሉ የአፍሪካ አገራት ድህነትን በግማሽ ለመቀነስ የተቀመጠውን የልማት ግብ ለማሳካት በመልካም መንገድ ላይ መሆናቸውን የቡድን ስምንቱ አገራት ጥናት ጠቁሞ አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገራትም ከግቡ ለመድረስ ለውጥ እያሳዩ መሆናቸውን ገልጿል።

ቡድን ስምንት አገራት ግምገማውን ያካሄዱት በተለይ ድህነትንና እርሃብን በግማሽ ዝቅ ለማድረግ ፣ የህጻናትን ሞት ለመቀነስና የእናቶችን ጤና ለማሳደግ በተቀመጠው የልማት ግቡ ላይ መሆኑንም ተጠቁሟል።